መልእክት ሁለት

**ለእውነተኛው አንድነት ከራሳችን ውስጥ ለመውጣት**
**እና ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ለመግባት በእውነት መቀደስ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዮሐ. 17፡14-24

I. **እውነት መለኮታዊው ብርሃን በመጽሐፍ ቅዱስ ሐቆች ላይ ማብራቱና የእነዚህን ሀቆች ሰማያዊ፣ መንፈሳዊ ራእይ ወደ ማንነታችን ውስጥ በትዕይንት መልክ ማስተላለፉ (televising) ነው፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እውነት እንዲህ አይነቱን "ሰማያዊ ቴሌቪዥን" ያመለክታል፦**

ሀ. ሁሉም መለኮታዊ ሐቆች በቃሉ ውስጥ አሉ፣ ወደ እኛ የሚተላለፉትም በቃሉ በኩል ነው፤ መንፈስ በቃሉ ላይ ሲያበራ፣ ሰማያዊው ቴሌቪዥን ይኖረናል፤ ብርሃኑ በቃሉ ውስጥ ባሉ ሐቆች ላይ ያበራል፣ የእነዚህንም ሐቆች ሰማያዊ ራእይ ወደ ማንነታችን ውስጥ ያስተላልፋል፣ እኛም እውነቱን እናውቃለን—ሐዋ. 26፡16፣ 19፤ ኤፌ. 1፡17-18።

ለ. መንፈስ የእውነት መንፈስ፣ የእውነታ መንፈስ ተብሏል (ዮሐ. 14፡17)፤ የእውነታ መንፈስ መንፈሳዊ ነገሮች ወደ ማንነታችን ውስጥ በትዕይንት መልክ የሚተላለፉበት "ሰማያዊው ኤሌክትሪክ" ነው፤ ወልድ የሆነውንና ያለውን ሁሉ ለእኛ እውን በማድረግ (1፡14፣ 17፤ 14፡6) "ወደ እውነታ ሁሉ" (16፡13) ይመራናል፦

ሐ. የእውነት መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ በተዘገቡትና በሚገኙት መንፈሳዊ ሐቆች ላይ ሲያበራ፣ እውነትን፣ እውነታን እንቀበላለን፤ ቃሉን ያለ መንፈስ ማብራት ካነበብን፣ ሊኖረን የሚችለው አስተምህሮ ወይም "የዜና ዘገባዎች" እንጂ እውነቱ፣ እውነታው፣ ወይም ራእዩ አይደለም—ተዛ. ኢዮብ 42፡5፣ ዮሐ. 5፡39-40፤ 2 ቆሮ. 3፡6።

መ. እውነት የብርሃን ማብራት፣ የብርሃን መገለጥ ነው፤ በሌላ አነጋገር፣ እውነት ብርሃን ሲገለጥ ነው፤ ብርሃን የእውነት ምንጭ በመሆኑና እውነት የብርሃን ውጤት በመሆኑ ምክንያት፣ በብርሃን ስንመላለስ፣ እውነቱን በተግባር እየተለማመድን ነው—ዮሐ. 1፡4-5፣ 7-9፣ 12-13፤ 8፡12፤ 14፡6፤ 1 ዮሐ. 1፡5-6፤ 2 ዮሐ. 4፤ 3 ዮሐ. 3-4።

ሠ. ጌታ ብርሃን፣ እውነት እና ቃል ነው፤ እውነትም ጭምር የሆነው ቃሉ ብርሃን ይሰጣል፣ ምክንያቱም በቃሉ ውስጥ ብርሃን አለና—ዮሐ. 8፡12፤ 14፡6፤ 17፡17፤ መዝ. 119፡105፣ 130።

ረ. እውነት የብርሃን—የሕይወት ብርሃን የሆነው—ማብራት ስለሆነ እውነት፣ ብርሃን እና ሕይወት የማይነጣጠሉ ናቸው፤ መለኮታዊው ብርሃን ወደ ውስጣችን ሲያበራ፣ በውስጣችን እውነት ይሆናል፣ ወደ ማንነታችንም ውስጥ ሕይወትን ያካፍላል—ዮሐ. 8፡12፣ 32፣ 40፤ 12፡35-36፣ 46፤ 14፡6።

II. **የእውነት ሁለት አገልግሎቶች አሉ፦**

ሀ. እውነቱ አሉታዊ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ እኛን አርነት በማውጣት ከኃጢአት እስራት አርነት ያወጣናል— 8፡32፣ 36።

ለ. እውነቱ እኛን በእግዚአብሔር ንጥረ-ነገር በማጥለቅለቅ፣ በስፍራና በባህሪ ይቀድሰናል—17፡17፤ ኤፌ. 5፡26።

III. **በቃሉ ውስጥ እውን የሆነልን እና ወደ ማንነታችን ውስጥ እየተካፈለና እየሰረጸን ያለው ሦስታንዱ አምላክ አርነት የሚያወጣንና የሚቀድሰን እውነት ነው፦**

ሀ. ከውስጥ ባዶነት እየተሰማን ስናዝን ወይም ሲደብተን፣ ራሳችንን መክፈትና ወደ ቃሉ መምጣት እንችላለን፤ ለጥቂት ጊዜ ካነበብን በኋላ፣ የሆነ ነገር በውስጣችን ብድግ ይላል፣ የጌታንም መገኘት እንደሰታለን—መዝ. 119፡25፣ 37፣ 40፣ 50፣ 88፣ 93፣ 107፣ 149፣ 154፣ 156፣ 159።

ለ. ቃሉን በዚህ ባለ መንገድ በመውሰድ፣ አንዳች የጌታ የሆነ ነገር ወደ ውስጣችን ይሠራል፤ ይህ የሦስታንዱ አምላክ መኖር፣ መንቀሳቀስ፣ መሥራት እና እኛን የመለየቱ እውነታ ነው።

ሐ. በየማለዳው በተጻፈው ቃል ውስጥ ያለውን ሕያዉን ቃል መንካት እና ወደ ማንነታችን ውስጥ እንደ ሚተገበረው ቃል በመለኮታዊው እውነታ፣ በሂደት ባለፈው ሦስታንዱ አምላክ መሰረጽ እንችላለን—ዮሐ. 1፡1፤ 10፡35፤ 5፡39-40፤ 6፡63፤ ኤፌ. 5፡26፤ 6፡17-18፤ መዝ. 119፡15፦

1. የዚህ የእግዚአብሔር ንጥረ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ መተላለፍ እንደ ንዴት፣ ቅናት፣ ጥላቻና ትዕቢት ካሉ አሉታዊ ነገሮች ነጻ ያወጣናል፤ ከየትኛውም አይነት ውሸት ነጻ ያወጣናል፣ እኛም እውነተኛ መፈታት፣ እውነተኛ ነጻነት ይኖረናል።
2. ነጻ ስንወጣ ሳለ፣ በስፍራ ብቻ ሳይሆን በባህሪም ጭምር እየተቀደስን፣ እየተለየን፣ ለእግዚአብሔር ቅዱስ እየተደረግን ጭምር ነው፤ የእርሱ የራሱ ውስጠ-ነገር ወደ ውስጣችን ስለተሠራ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንሆናለን።

መ. በየዕለቱ በዚህ መንገድ ወደ ቃሉ መምጣት ያስፈልገናል፤ በየማለዳው ቢቻል ደግሞ በሌላ ጊዜያትም ጭምር ወደ ቃሉ መምጣት ያስፈልገናል።

ሠ. ቃሉ በመንፈሳችን ውስጥ ካለው ሕያው መንፈስ ጋር ሲዋሐድ፣ በእግዚአብሔር ውስጠ-ነገር እንቀደሳለን።

ረ. በዚህ መንገድ ቃሉን በመንካት፣ እግዚአብሔር ዕለት በዕለት ወደ ውስጣችን ይጨመራል፤ በውጤቱም ሁለመናችን በእግዚአብሔር ይሞላል ከእርሱም ጋር አንድ እንደረጋለን።

ሰ. ዋናው ፍላጎታችን ሕያው የሆነው ሦስታንድ አምላክ በተጻፈው ቃል፣ በሕያዉ ቃል እና በሚተገበረው የእግዚአብሔር ቃል በኩል ወደ እኛ ውስጥ መሰረጹና መሠራቱ ነው።

## IV. በእውነት ቃል መቀደስ የክፍፍል መንስኤዎችን በማስወገድ አንድነትን ያመጣል፤ እውነት ይቀድሳል፣ መቀደስ ደግሞ አንድነትን ያመጣል—ዮሐ. 17፡14-24፡-

ሀ. ጌታ ኢየሱስ፣ ወልድ፣ እውነት ነው፤ መንፈስ የእውነት መንፈስ ነው፤ የአብ ቃል እውነት ነው—1፡14፣ 17፤ 14፡6፣ 17፤ 17፡17፤ 1 ዮሐ. 5፡6፡-

1. አብ በወልድ አካል ለብሷል፣ ወልድ እንደ እውነት መንፈስ እውን ሆኗል፣ መንፈሱ ከቃሉ ጋር አንድ ነው—ቆላ. 2፡9፤ 1 ዮሐ. 14፡17፤ 16፡13፤ ኤፌ. 6፡17-18።
2. በተከፈተ ልብና በተከፈተ መንፈስ ወደ ቃሉ በመጣን ጊዜ ሁሉ፣ ቃሉንም መንፈሱንም እንደ እውነት ወዲያውኑ እንነካለን።

ለ. የሚቀድሰው ቃል፣ የሚቀድሰው መንፈስ፣ የሚቀድሰው ሕይወት እና የሚቀድሰው አምላክ እነዚህ ሁሉ አንድ ናቸው፤ ስለዚህ፣ እየተቀደስን ከሆነ፣ የክፍፍል መንስኤዎች ሁሉ ስለተወገዱ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ አንድ ነን።

ሐ. በዮሐንስ 17፡17-23 ውስጥ መቀደስ እውነተኛውን አንድነት እንደሚያመጣ እናያለን ምክንያቱም ይህ አንድነት በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ይጠብቀናልና፤ ቁጥር 21 እንዲህ ይላል፣ "ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፤... አንተ፣ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፣ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ"፡-

1. አንድ ለመሆን በ "እኛ" ውስጥ፣ ማለትም፣ በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ መሆን ያስፈልገናል።
2. በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ የመሆኛው ብቸኛው መንገድ ሁሉንም የክፍፍል መንስኤዎች በሚያስወግደው በሚቀድሰው እውነት ነው።
3. በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ በመጠበቅ አንድ ነን፣ ከሦስታንዱ አምላክ ውስጥ በወጣን ጊዜ ሁሉ ግን ወዲያውኑ እንከፋፈላለን።
4. በየማለዳው ጌታን መገናኘት፣ ሕያዉን ቃል መንካት እና መለኮታዊው እውነታ ወደ ማንነታችን ውስጥ ሊሰረጽ ያስፈልገናል፤ ጌታን በዚህ መንገድ ስንገናኝ፣ የክፍፍል መንስኤዎች ድል ይነሣሉ።
5. በውስጣችን ያሉ የክፍፍል መንስኤዎች በሚቀድሰው እውነት ሲገደሉ፣ ወደ እውነተኛው አንድነት እንመጣለን፣ መቀደስ በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ይጠብቀናልና።
6. በእውነቱ ቃል መቀደስ የሦስታንዱ አምላክ አንድነት መተለቅ የሆነውን የክርስቶስን አካል አንድነት ያመጣል—ቁ. 21።

## V. አራት የክፍፍል መንስኤዎች አሉ፡-

ሀ. ከእነዚህ መንስኤዎች የመጀመሪያው ዓለማዊነት ነው፤ ዓለምን በሆነ ገጽታ እስከወደድን ድረስ፣ ያ የዓለማዊነት ገጽታ የክፍፍል ምክንያት ይሆናል—ቁ. 14-16፣ 18፤ 1 ዮሐ. 2፡15-17፤ 5፡19።

ለ. ሌላኛው የክፍፍል መንስኤ ምኞትን ለማሳካት አጥብቆ መፈለግ ነው፤ ጌታን በቃሉ በኩል ስንነካውና ራሱን ወደ ውስጣችን እንዲሰርጽ ስንፈቅድለት፣ ወደ ውስጣችን የተካፈለው እውነት ምኞታችንን ለማሳካት አጥብቀን መፈለጋችንን ይገድለዋል—ተዛ. ኢሳ. 14፡13።

ሐ. ሦስተኛው የክፍፍል መንስኤ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ነው፤ ምንም ለመሆን እና ክርስቶስን እንደ ብቸኛው ሰው፣ አጽናፍ-ዓለማዊ ፊተኛ ስፍራ እንዳለው ማንነት ከፍ ከፍ ለማድረግ መፍቀድ አለብን—ቆላ. 1፡18፤ 2 ቆሮ. 4፡5፤ 3 ዮሐ. 9-11።

መ. አራተኛው የክፍፍል መንስኤ አመለካከቶች እና ጽንሰ-ሃሳቦች ናቸው፤ አመለካከታችንን መያዝ ሳይሆን በቀላሉ የጌታን ግብ መከታተል አለብን፡- ለቤተ ክርስቲያን መገንባት የክርስቶስ እንደ ሕይወትና እንደ ሁሉ ነገር ምለሳ—ማቴ. 16፡21-24፤ ተዛ. ራእ. 3፡14።

## VI. ከራሳችን ውስጥ ወጥተን ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ስንገባ፣ አንድ ነን እንዲያውም ወደ አንድ ፍጹም እንደረጋለን፡- ዮሐ. 17፡11፣ 17፣ 21-23፡-

ሀ. በራሳችን አራቱ የክፍፍል መንስኤዎች አሉን፤ በእኔነት ውስጥ ከቆየን ከእነዚህ አራት ነገሮች ማምለጥ አንችልም።

ለ. መቀደስ ከራሳችን ወጥተን ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ መግባት እና ክርስቶስ በእኛ ውስጥ እንዲኖር መፍቀድ ማለት ነው፤ በዚህ መንገድ ወደ አንድ ፍጹም ተደርገናል—ቁ. 21-23።

ሐ. ይህ መቀደስ የሚከናወነው እውነት በሆነው ቃሉ እና የእውነት መንፈስ በሆነው በመንፈስ ነው፡-

1. በየማለዳው ወደ ቃሉ ስንመጣ፣ በውጪ ቃሉን እንነካለን፣ በውስጥ ግን መንፈስ ይነካናል፤ ሁለቱም እውነታ በሆኑት በቃሉና በመንፈሱ እንቀደሳለን።
2. ቃሉን አብዝተን ስንነካ እና መንፈስ አብዝቶ ሲነካን፣ አብዝተን ከራሳችንን እንወጣለን፤ ከአንድ የመኖሪያ ስፍራ፣ ከእኔነት፣ ወደ ሌላ የመኖሪያ ስፍራ፣ ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ እንሸጋገራለን።
3. በእኔነት ውስጥ ዓለማዊነት፣ ምኞትን ለማሳካት አጥብቆ መፈለግ፣ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ እና አመለካከቶችና ጽንሰ-ሃሳቦች ስላሉ በየቀኑ ይህንን እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልገናል።
4. ያለማቋረጥ ቃሉን ከነካንና መንፈስ ቀን በቀን እንዲነካን ከፈቀድን፣ እንቀደሳለን፤ ማለትም፣ ከራሳችን፣ ከአሮጌው የመኖሪያ ስፍራችን ወጥተን ወደ ሦስታንዱ አምላክ፣ ወደ አዲሱ የመኖሪያ ስፍራችን ውስጥ እንሸጋገራለን።
5. አንዴ ከራሳችን ከወጣን፣ እንቀደሳለን፣ ከክፍፍል መንስኤዎች እንለያለን፣ ለእግዚአብሔር መለየት ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ውስጥም ጭምር እንለያለን።
6. እውነተኛው አንድነት እንዲኖረን፣ አስቀድመን ከራሳችን መውጣትና ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ መግባት አለብን (ቁ. 17፣ 21)፤ ከዚያም ክርስቶስ በእኛ እንዲኖር መፍቀድ አለብን (ቁ. 23)፡-
   ሀ. ይህ ፍጹም የተደረገ አንድነት እውነተኛው ግንባታ ነው፤ ይህ በሕይወት ማደግ ነው—ኤፌ. 4፡16።
   ለ. በሕይወት ማደግ ማለት ከራሳችን መውጣትና ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ መግባት እና ክርስቶስ በእኛ እንዲኖር መፍቀድ ማለት ነው፤ ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ከገባን እና ክርስቶስ በእኛ እንዲኖር ከፈቀድን፣ በየትኛውም አጥቢያ ካሉ ቅዱሳን ጋር አንድ መሆን እንችላለን።

መ. "እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፣ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ"—ዮሐ. 17፡23፡-

1. አንድ ወደ መሆን ፍጹም መደረግ ማለት ከዓለማዊነት፣ ምኞትን ለማሳካት አጥብቆ ከመፈለግ፣ ራስን ከፍ ከፍ ከማድረግ እና ከአመለካከቶችና ከጽንሰ-ሃሳቦች መዳን ማለት ነው።
2. "እኔ በእነርሱ—ይህ ማለት ወልድ በውስጣችን እየኖረ እና እየተንቀሳቀሰ ነው ማለት ነው።
3. "አንተም በእኔ"—ይህ ማለት አብ በወልድ ውስጥ እየኖረ እና እየተንቀሳቀሰ ነው ማለት ነው።
4. በሌላ አነጋገር፣ ወልድ በእኛ ውስጥ እየኖረ እና እየተንቀሳቀሰ ሳለ፣ አብ በእርሱ ውስጥ ይኖራል ይንቀሳቀስማል፤ በዚህ ሁለት እጥፍ መኖርና መንቀሳቀስ፣ አንድ ወደ መሆን ፍጹም እንደረጋለን፣ አብን በክብር እንገልጠዋለን።

ሠ. ምኞትን ለማሳካት አጥብቆ መፈለግ በዮሐንስ 17፡21 ተመላክቷል፤ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ በቁጥር 22፤ እና ጽንሰ-ሃሳቦችና አመለካከቶች በቁጥር 23፡-

1. በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ምኞትን ለማሳካት አጥብቆ መፈለግ የለም፣ በአብ ክብር ውስጥ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ የለም፣ ክርስቶስ በሚኖርበትና በሚገዛበት ስፍራም አመለካከቶች የሉም።
2. በሂደት ባለፈው ሦስታንዱ አምላክ መለኮታዊና ምሥጢራዊ ክልል ውስጥ ምኞትን ለማሳካት አጥብቆ መፈለግ ይዋጣል፣ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ይጠፋል፣ ጽንሰ-ሃሳቦች እና አመለካከቶችም ይገደላሉ፤ በዚህ ሰይጣን-ባደራጀው ዓለም ውስጥ ያለው የክፍፍል ክፋት የለም (ቁ. 15)፤ በዚህ ፋንታ፣ እውነተኛው አንድነት አለ።

ረ. እውነተኛው አንድነት በአብ ውስጥ መኖር፣ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ እንዲኖር መፍቀድ እና በአብ ክብር፣ በመገለጡ ውስጥ መኖር ነው—ቁ. 22፣ 24፡-

1. ለአብ መገለጥ፣ ለክብሩ ከራሳችን ወጥተን ወደ ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ መግባት እና በእርሱ ውስጥ መቆየት ያስፈልገናል።
2. እውነተኛው ግንባታ፣ አንድነት፣ የሚቻል የሚሆነው በሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ብቻ ነው፣ ይህ የሚሆነውም ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው፤ ያኔ አብን በክብር መግለጥና እውነተኛውን አንድነት መለማመድ እንችላለን።

© 2021 Living Stream Ministry